# ተማሪዎችን በቤት ውስጥ መደገፍ አጸደ ሕፃናት

*በመጀመሪያ በሃዋርድ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የተዘጋጀ እና ለዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ*

## አጭር መግለጫ

ይህ መመሪያ ት/ቤቶች በCOVID-19 ምክንያት በተዘጉበት ወቅት ተማሪዎች በትምህርት ተግባሮች ላይ እንዲቆዩ ለማድረግ ሀሳቦችን እንዲሰጥ የተዘጋጀ ነው። የተዘረዘሩት ተግባራት ልጆቻችን በቤታቸው በሚውሉበት ጊዜ በአዕምሯቸው ንቁ ሆነው እንዲቆዩ ለመርዳት የታሰቡ ናቸው። የተግባር ሀሳቦቹ በት/ቤቶች የሚሰጠውን የመጀመሪያ ደረጃ የመማር-ማስተማር ሂደትን አይወክሉም። የመጀመሪያ ደረጃ የመማር-ማስተማር ምርጥ ተሞክሮዎች ተማሪዎች ወደ ት/ቤት በሚመለሱበት ጊዜ የሚታዩ ናቸው።

ልጆች በቤታቸው የሚያከናውኗቸው ተግባሮችና ሥራዎች እንደምዘና አገልግሎት የሚውሉ ወይም ወደ ተማሪዎች ውጤቶች (ግሬድስ) የሚቆጠሩ አይሆኑም። ቤተሰቦች ዝርዝሩን አንብበው ጠቃሚና ተደራሽ የሆኑ አማራጮችን መምረጥ ይኖርባቸዋል። ተግባራቱ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሠሩ ይችላሉ።

## ለምሳሌ የቀረበ የየዕለት ጊዜ ሰሌዳ

| | | |
|---|---|---|
| 8:00-9:00 | **መንቃት እና መዘጋጀት** | ቁርስ መብላት፣ መልበስ እና ለቀኑ መዘጋጀት |
| 9:00-10:00 | **የትምህርት ሰዓት** | ከዚህ በታች ካለው ዝርዝር ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ አማራጮችን ምረጡ። |
| 10:00-10:30 | **ነፃ ምርጫ** | እንደ ሌጎስ፣ ስዕል፣ ምግብ ማብሰል፣ ፐዝሎች፣ የቦርድ ላይ ጨዋታዎች ያለ ተግባርን ምረጡ። |
| 10:30-11:00 | **የስክሪን (የቲቪና ሞባይል) ጊዜ** | ከዚህ በታች ካሉት የስክሪን-ተኮር ተግባሮች ዝርዝሮች ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ መምረጥ። |
| 11:00-12:00 | **ምሣ እና ነፃ ጊዜ** | ምሣ ብሉ፣ ለእግር መንገድ ወይም ውጭ ለመጫዎት ሂዱ |
| 12:00-1:00 | **የትምህርት ሰዓት** | ከዚህ በታች ካለው ዝርዝር ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ አማራጮችን ምረጡ። |
| 1:00-1:30 | **ነፃ ምርጫ** | እንደ ሌጎስ፣ ስዕል፣ ምግብ ማብሰል፣ ፐዝሎች፣ የቦርድ ላይ ጨዋታዎች ያለ ተግባርን ምረጡ። |

| | | |
|---|---|---|
| 1:30-2:00 | **ንባብ** | አንድ መጽሐፍ ማንበብ ወይም ከዚህ በታች ካሉት አቅርቦቶች አንድ የኦንላይን መጽሐፍን ምረጡና አንብቡ። |
| 2:30-2:00 | **የከቤት ውጭ ጊዜ** | ለእግር መንገድ ወይም ውጭ ለመጫዎት ሂዱ |
| 2:30-3:00 | **የስክሪን (የቲቪና ሞባይል) ጊዜ** | ከዚህ በታች ካለው የስክሪን-ተኮር ተግባሮች ዝርዝር ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ምረጡ። |
| 3:00-4:00 | **ነፃ ምርጫ** | እንደ ሌጎስ፣ ስዕል፣ ምግብ ማብሰል፣ ፐዝሎች፣ የቦርድ ላይ ጨዋታዎች ያለ ተግባርን ምረጡ። |

# የተግባር ምርጫዎች

እያንዳንዱ የትምህርት ዘርፍ "የምርጫ ቦርድ" አማራጮች አሉት። በእያንዳንዱ ቀን ከተወሰኑ የትምህርት ዘርፎች የተለያዩ ተግባራትን ለመምረጥ ሞክሩ። እነዚህ አማራጮች የአካላዊ እንቅስቃሴ፣ የመጽሐፍት ንባብ፣ እና የቴክኖሎጅ ጠቀሜታ፣ የመስመር-ላይ አቅርቦቶችን/ግብዓቶችን እና የቴሌቪዥን ፕሮግራም ዕድሎችን ያካትታሉ። ልጆችዎ ስለሚሠሯቸው ተግባራት ከልጆችዎ ጋር መነጋገር የንግግር ክህሎቶቻቸውን እና ግንዛቤያቸውን ለማጠናከር ይረዳል።

ልጆችዎ በየቀኑ የተለያዩ ተግባራትን እንዲመርጡ እና በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ቀጣይነትን ለማበረታታት የሚከተለውን ሠንጠረዥ ተጠቀሙ (ከሃዋርድ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የተገኘ እና ለዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ)፦

| ርዕስ | አማራጭ 1 | አማራጭ 2 | አማራጭ 3 | አማራጭ 4 |
|---|---|---|---|---|
| **የቋንቋ ጥበባት** | አንድ ታሪክን አንብቡ/አዳምጡ። የቤታችሁ ፊትለፊት ያለውን የእግር መንገድ (ሳይድወክ)፣ ቾክ፣ ማርከር፣ ክራዮን ወይም ቀለም በመጠቀም ስለታሪኩ ስዕልን ሳሉ። | "Tongue Twisters"ን እያላችሁ በድምጻቸው ተዝናኑ። -Freshly fried flying fish -She sells seashells by the seashore<br>-Ned's knapsack strap snapped<br>-Rubber baby buggy bumpers<br>አዳዲስ መላስ ጠምዛዥን (Tongue Twisters) ፍጠሩ! | የሚስባችሁን መረጃ ሰጭ መጽሐፍን አንብቡ/አዳምጡ። መጽሐፉን ካነበባችሁ በኋላ ስለተማራችኋቸው እውነታዎች ጻፉ ወይም ሳሉ። | "Tic-Tac-Toe Blends" ን ተጫዎቱ የtic-tac-toe ቦርድ ሳሉ። እያንዳንዱ ተጫዋች "X"ን ወይም "o"ን ከመምረጥ ይልቅ የፊደል ጥምር (letter blend፡ bl, cl, br, tr, fl, gl, pl, scr, sk,) ይመርጣል። እያንዳንዱ ተጫዋች በመረጠው የፊደል ጥምር (letter blend) የሚጀምር ቃልን ማለትና ጥምረቱን ባዶ ቦታ ላይ መጻፍ አለበት። |
| **ሒሳብ** | ወደ ቅርጸች አደን ውጡ። ስንት ክቦች፣ ሦስት ማእዘኖች፣ ካሬዎች እና አራት ማእዘኖች አገኛችሁ? | በቤቱ ውስጥ ያሉ ነገሮችን ቁጠሩ። ስንት ሰዓቶች አሏችሁ? ስንት የቤት ውስጥ እቃዎች (ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ሶፋ እና የመሳሰሉት) አሏችሁ? | እንደ ካልሲዎች፣ ሲቲከሮች እና አሻንጉሊቶች ያሉ ነገሮችን በምድብ በምድብ አስቀምጧቸው እና የትኛው ምድብ ብዙ የትኛው ትንሽ ነገሮች እንዳሉት ተነጋገሩ። | የተለያዩ ነገሮችን በማጣመር በስንት መንገዶች አንድን ቁጥር (10 ወይም ከዚያ በታች) መሥራት ትችላላችሁ? |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ሳይንስ** | የቤት የሳይንስ መዋዕል (ጆርናል) አዘጋጁ። በእያንዳንዱ ቀን በጽሑፍ ወይም በስዕል መዋዕልን አክሉ። ምን አስገረማችሁ? ምን ታዘባችሁ (አያችሁ፣ ሰማችሁ፣ ተሰማችሁ)? አንድ ኢ-ልብወለድ የሆነ የሳይንስ መጽሐፍ አንብቡ ወይም አዳምጡና ስለተማራችሁት አዲስ ነገር ጻፉ። | በቤታችሁ ውስጥ የቤት እንስሳ (ፔት) ወይም የእንስሳ አሻንጉሊት አላችሁ? የተቻላችሁን ያህል ዝርዝር በመጠቀም ስለእንስሳው የሰውነት ክፍሎች እና ስለእያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ጥቅም ስዕል ስላችሁ በስዕሉ ላይ አመልክቱ (ሌብል አድርጉ)። ለቤት ውጪ አንዳች እንስሳትን ታያላችሁ? ምን እያደረጉ አያችዋቸው? ስለሚያደርጉት ነገር ጻፉ። ምን ባሕሪን አያችሁ? | ምክንያትና ውጤቱን አስቡት። አንድን ኳስ በቀስታ ብትገፉት (ብታንከባልሉት) ምን የሚሆን ይመስላችኋል? አንድን ኳስ በኃይል ብትገፉት (ብታንከባልሉት) ምን የሚሆን ይመስላችኋል?<br><br>ምን ሆነ? እንዲያ እንዲሆን ያደረገው ምንድን ነው?<br>ሌላ ምን አሻንጉሊቶችን በተለያዩ መንገዶች መግፋት ወይም መጎተት ትችላላችሁ? ስለምክንያቱና ውጤቱ በቤት የሳይንስ መዋዕላችሁ ላይ ጻፉ። | በቤታችሁ ውስጥ ወይም በውጪ (*በአዋቂ ፈቃድ*) የምታዩአቸውን የተለያዩ ነገሮችን በቅርበት አስተውሉ። ነገሩን ለመግለጽ ስንት ቃላት መጠቀም ትችላላችሁ? ቀለሙን፣ ገጽታውን፣ መጠኑን፣ ቅርጹን ወይም ሽታውን ለመግለጽ ትችላላችሁ? ሌሎች መለያ ባሕሪዎች አሉን |
| **ሶሻል ስተዲስ** | የሕጎች ዝርዝርን ፍጠሩ። ሕጎቹ ለቤተሰባችሁ፣ ት/ቤታችሁ ወይም ማኅበረሰባችሁ ሊሆኑ ይችላሉ። እያንዳንዱን ሕግ እየፈጸማችሁ ያላችሁባቸውን ስዕሎች ሳሉ። | ልጆች እያሉ ሕይወታቸው ምን ይመስል እንደነበር ከአንድ አዋቂ ጋር ተነጋገሩ። የእነሱ የልጅነት ሕይወት ከእናንተ ሕይወት ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል እና እንደሚለያይ አወዳድሩ። | ቤታችሁን ፈትሹ እና እቃዎች እንዴት እንደተሠሩ እና ከየት እንደመጡ ለዩ/እወቁ። | የምትወዱትን ቦታ (የመጫወቻ ቦታ፣ ቤት፣ ማኅበረሰብ) ካርታን ሥሩ። |
| **ተያያዥ ሥነ-ጥበባት** | *ሙዚቃ*- የተለያዩ የቤት እቃዎችን በመጠቀም የምት ዓይነቶችን (beat እና rhythm) ልዩነት ፈትሹ። ጮክ እና ለስለስ ያሉ ኖታዎችን እና ድምጾችን ያካተተ ሙዚቃን ፍጠሩ። | *ሙዚቃ*- ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ድምጽን (ፒችን) ለመፈተሽ ድምጻችሁን ተጠቀሙ። ድምጻችሁን ከሌላ ሰው ድምጽ ጋር አወዳድሩ እንዲሁም አነጻጽሩ። | *የቤተ-መጽሐፍት ሚዲያ*- የስዕል መጽሐፍትን፣ የምዕራፍ መጽሐፍትን፣ መጽሔቶችን እና ኮሚኮችን ጨምሮ የተለያዩ የንባብ ግብዓቶችን (ማቴሪያሎችን) ምረጡ። በልብ ወለድ እና ኢ-ልብ ወለድ መካከል ምን ልዩነትን አስታዋላችሁ? | *የሰውነት ማጎልመሻ (PE) እና ጤና*- (በአዋቂ ፈቃድ) የመረጡትን የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለ30 ደቂቃ ሥሩ። |
| **ተያያዥ ሥነ-ጥበባት** | *የመማር-ማስተማር ቴክኖሎጂ*- የመጠሪያ እና የአያት (ላስት) ስማችሁን፣ የተጠቃሚ ስማችሁን/የይለፍ ቃላችሁን እና/ወይም ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸው ቃላትን በኮምፒውተር ቃላት መሠነጃ ባዶ ገጽ ላይ መተየብ (ታይፕ ማድረግ) ተለማመዱ። | *የሰውነት ማጎልመሻ (PE) እና ጤና* የዳንስ ፓርቲ አድርጉ። በምትወዱት ሙዚቃ ደንሱ። | *ሥነ-ጥበብ*- በምትወዷቸው ነገሮች ላይ በመመሥረት አንድ ጭብጥ ያለው ፓርክን ንደፉ። የምትወዷቸውን የመሽከርከሪያ ዓይነቶችን (rides) ንድፍ ሳሉ። እዚያ በምትሆኑበት ጊዜ ምን ልትበሉ ትችላላችሁ? ምን ማሳመሪያዎች ወይም እይታዎች ሊኖሩ ይችላሉ? | *የቤተ-መጽሐፍት ሚዲያ*- ቅመማ ቅመሞችን፣ የታሸጉ የቆርቆሮ ምግቦችን እና ሌሎች ነገሮችን በእንግሊዝኛ ፊደል ቅደም ተከተላቸው በማስቀመጥ ተለማመዱ። |

## ዲጅታዊ መረጃዎች

DENVER PUBLIC SCHOOLS | Academics

*በዲጅታዊ መንገድ ሊገኙ የሚችሉ የተወሰኑ ግብዓቶች እዚህ ይገኛሉ፦*

- Scholastic Learn at Home
- PBSKids
- የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች ዲጂታዊ ቤተመጽሐፍት
- የዴንቨር የሕዝብ ቤተመጽሐፍት ታሪኮችንና ዘፈኖችን በስልክ በእንግሊዝኛ፣ በስፓኒሽኛ፣ በአማርኛ እና በቬትናምኛ የሚገኝ አገልግሎት
- የDPS' አካዳሚክ ቴክኖሎጂ ዝርዝር፡
    - የትምህርት ቤት ዝርዝሮችን (Breakdowns) → የእናንተን ት/ቤት → ሂድ ምረጡ!
    - "የወላጆች ስምምነት ያስፈልጋል" ትር፦ ግብዓቶች በወላጅ ስምምነት አማካኝነት በት/ቤታችሁ ይፈቀዳሉ
    - "የወላጆች ስምምነት ይጠየቃል" ትር፦ በዲስትሪክት የተፈቀዱ ግብዓቶች

## ለስፓኒሽኛ ተናጋሪ ወላጆች የተግባር ሀሳቦች

- Las Provincias
- Bebesymas
- Sapos Y Princesas

## ትምህርታዊ ቴቪ

PBS የተለያዩ ትምህርታዊ ቴቪ ቻናሎች አሉት። በዴንቨር አካባቢ PBSን መጠቀም የምትችሉት እንዲህ ነው።

- በአንቴና
    - Rocky Mountain PBS፦ ቻናል 6.1
    - RMPBS KIDS፦ ቻናል 6.2
- በኬብል ቴቪ (ኮምካስት)
    - Rocky Mountain PBS፦ ቻናል 6 እና 658
    - RMPBS KIDS፦ ቻናል 245
    - Create/World*፦ ቻናል 248
    - በጥያቄ፦ ቻናል 1 ("የእርስዎ ኮሎራዶ")
- ሳተላይት (DIRECTV)
    - Rocky Mountain PBS፦ ቻናል 6
- ሳተላይት (ዲሽ ኔትዎርክ)
    - Rocky Mountain PBS HD: ቻናል 6